# " ዲሲና ደደቢት፤ ኢምባሲ ፊት ለፊት! "



*የጐንቻው!*

*ዋሺንግተን ዲሲ ‘ ኢትዮጵያ ኢምባሲ’ የመሸገው ሽፍታ፤*

*ከውጭ ሱፍ ለብጦ ውስጡ ግን ድሪቶ የደደቢት ኩታ፤*

*ዘር ስንዝር ያሰ’ፋው ነጠላ፤ ጥብቆ ቋጠሮው ተፈታ፤*

*ፍራት ቢቆፈኘው ደም በለመደ እጁ በሽጉጥ ሊፍታታ፤*

*በዲፕሎማሲ ስም ሽፋፍነው ያጣፉት ገመናው ተረታ፤*

*ግርማ ጃዝ ያሉት ‘ዘብ’ ሶስቴ አባረቀና ከሽፎበት ተገታ።*

*ወጣት ጀግኖች አይቶ ባንዲራ ሰንድቀው ሲመጡ በተርታ፤*

*በግፍ ለታሰሩት፤ጅምላ ለተጣሉት፤ሰላም ሊጠይቁ ፍትህ ባሉ እፎይታ፤*

*ደንቆሮ፤ጋግርታም አፍ-ላንቃው ተሳስሮ ደም በለመድ እጁ አነዘረ ቃታ፤*

*‘ወዲ ወያኔ ሰብ’ መግደል ዛር የናጠው ኋሊት እያስደኸ በጥይት እሩምታ፤*

*ደግኖም ተኮሰ ፍርሃት ብርክ ይዞት ጥላቻ ተክህኖ የአጋዚው አውታታ፤*

***‘ባርቆበት’ ሶስቴ ጊዜ ‘ከሸፈ’ አራተኛው አጉብጦ ያለመው ግንባር እንዲመታ።***

*ጓዳ ቢደበቅም ሽንት- ቤት ቆልፎ አላገኘም ፋታ፤*

*ፍጥኝ ተጠርንፎ ግርማ አላስጣለውም ታቅፎ መከታ፤*

*እጅ ወደ ላይ ብሎ ‘ለጌታም ጌታ አለው’ ትጥቁን እሚፈታ፤*

*ተጠርዞ እጅ እግሩ ተጋዘ ደደቢት ሊቆዝም ጡረታ፤*

*ተቃውሞው ተሳክቷል! ዓለም ዘግቦታል! ቢቧልትም ዋልታ፤*

## *ድል ግን አይቀሬ ነው የምታ! የማታ!*

**ማስታዋሻ፡-**

*በዲሲ ኢትዮጵያ ኢምባሲ ተገኝተው በግፍ ለተረሸኑ የኦጋዴን ወገኖቻችን፤በጋቤላ ለሚገደሉትና ለሚሳደዱት በእስር ለሚሰቃዩት ሁሉ፤ብሶታቸውን ለማሰማት፤ ቁጣቸውን በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ ለመግለጽ በፍጹም ጀግንነት ለቆሙትየዲሲ ወጣቶች፤የወያኔ አጋዚ ቅጥር ነፈሰ ገዳይ፤የጥይት እሩምታ ሳይበግራቸው በጽናት ለታገሉት ምግባራቹህን፤ገድላችሁን ዓለም ዘግቦታል፤ተምሳሌነታችሁም በኢትዮጵያዊያን ላይ የጋለ የፍቅርና የድፍረት ክብሪት ጭሯልና ምስጋናም ክብርም ይገባቹሃል።*

*የጐንቻው!*